የሰ/መ/ቁ. 58822

መጋቢት 5 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጐስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዐቃቤ ሕግ ታደሰ ተስፋዬ - ቀረበ፡፡

**ተጠሪ፡-** አይንሽምስ ሁሴን አብደላ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ ለሰበር የቀረበው ክርክር በወንጀል ክስ ምክንያት በኤግዚቢትነት ተይዞ የቆየውና በኋላ ከወንጀሉ ክስ በነፃ ለተሰናበቱት ለአሁኑ ተጠሪ ይመለስ የተባለው የአፈር ወርቅ ይዞት በቆየው አካል በአሁኑ አመልካች ተሸጦ ከተገኘ ለወርቁ ባለቤት ሊከፈል የሚገባው ተሸጧል የተባለበት ዋጋ መሆን አለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪ 2512 ግራም የአፈር ወርቅ በህገወጥ መንገድ ደብቆ ሊያሣልፍ ሲል ተይዟል ተብሎ በቀረበበት የወንጀል ክስ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክርክርና ማስረጃዎቹን መርምሮ ወንጀሉን መፈፀሙ ተረጋግጧል ብሎ ጥፋተኛ በማድረግ በኤግዚቢትነት የተያዘው የአፈር ወርቅም እንዲወረስ ወስኖ የነበረ ቢሆንም ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሣኔ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በመሻር ከክሱ በነፃ እንዳዲሰናበት ፣ በኤግዚቢትነት ተይዞ የቆየው የአፈር ወርቅም ለአሁኑ ተጠሪ እንዲመለስለት ወስኗል፡፡

ይህ የከፍተኛው ፍ/ቤት ውሣኔ ይግባኝ ተብሎበት የተለወጠ ባለመሆኑ ኤግዚቢቱ ይመለስልኝ የሚለውን ጥያቄ የአሁኑ ተጠሪ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረበው ሲሆን የአሁኑ አመልካች ቀርቦ ሲጠየቅ የአፈር ወርቁን በወቅቱ በነበረው ዋጋ እክፍላለሁ የሚል መልስ ሰጥቷል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ አመልካች የአፈር ወርቁን ዋጋ እከፍላለሁ ያለውን ቢቀበሉትም የሚከፈለው በወቅቱ በነበረው ዋጋ ነው በሚለው ላይ ሣይስማሙ ቀርተዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የአሁኑ አመልካች ገንዘቡን የምከፍለው በወቅቱ በነበረው ዋጋ ነው ያለው ተገቢ አይደለም በማለት ታህሣሥ 10 ቀን 2000 ዓ.ም በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ዋጋው ታስቦ ለአሁኑ ተጠሪ መክፈል ይገባዋል የሚል ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ትዕዛዝ ላይ ይግባኙ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ግራቀኙ እንዲቀርቡ አድርጐ በጉዳዩ ላይ ካከራከረ በኋላ መርምሮ በሰጠው ፍርድ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠው ትዕዛዝ ጉድለት የለበትም በማለት አጽንቶታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ አመልካች የአፈር ወርቁን ዋጋ መክፈል ያለበት በወቅቱ በነበረው ዋጋ መሠረት ሣይሆን በኋላ ትዕዛዝ በተሰጠበት ጊዜ በነበረው የገበያ ዋጋ መሠረት ነው በሚል የተሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሠረት የቀረበ ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ ተብሎ በመታዘዙ ማመልከቻው ለአሁኑ ተጠሪ ተልኮ ቀርቦ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት ተጠሪ በጽሑፍ በሰጠው መልስ የአሁኑ አመልካች በወቅቱ የአፈር ወርቁ የተሸጠበትን ዋጋ እከፍላለሁ በማለት የጠየቀው ተቀባይነት ሊሰጠው አይገባም፣ ወርቁን በአይነት መመለስ ካልቻለ በጊዜው በወጣው የብሔራዊ ባንክ በሚሰጠው ዋጋ መሠረት መክፈል ይኖርበታል በማለት ተከራክሯል፡፡ በተጠሪ በኩል በጽሑፍ የተሰጠው መልስ ለአመልካች የተሰጠ ቢሆንም ከመዝገቡ እንደሚታየው በጽሑፍ ያቀረበው የመልስ መልስ የለም፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና የክርክሩ ይዘት ከዚህ በላይ እንደተመለከተው ሲሆን ይህ የሰበር ችሎቱም ጉዳዩን ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

የአሁኑ አመልካች ለአሁኑ ተጠሪ መክፈል የሚገባው የኤግዚቢቱ የአፈር ወርቅ ዋጋ በወቅቱ ሽጫለው የሚልበትን ዋጋ ነው ወይንስ በኋላ ፍ/ቤት ወርቁን መመለስ አለበት የሚል ትዕዛዝ በሰጠበት ጊዜ የነበረውን ዋጋ ነው? የሚለውን ዋናውን የክርክር ጭብጥ በተመለከተ፡-

የአሁኑ አመልካች ሐምሌ 27 ቀን 2002 ዓ.ም ተጽፎ ባቀረበው የሰበር ማመልከቻው ላይ በኤግዚቢትነት ተይዞ የቆየውን የአፈር ወርቅ ሊሸጠው የቻለው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁኑን ተጠሪ በወንጀሉ ጥፋተኛ በማድረግ መጋቢት 22 ቀን 1997 ዓ.ም ወርቁ እንዲወረስ በማለት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት መሆኑንና ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ወርቁ እንዳይሸጥ የሚል ትዕዛዝ ያስተላለፈው ወርቁ በውርስ ውሣኔው መሠረት እንዲሸጥ ከተደረገ በኋላ ሰኔ 15 ቀን 1997 ዓ.ም እንደሆነ የገለጹ ሲሆን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም የካቲት 29 ቀን 2002 ዓ.ም መሆኑን ገልጿል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ይህንን በሚመለከት በጽሐፍ ባመጣው መልስ ላይ የአሁኑ አመልካች ወርቁን የሸጠው መቼ ነው? ከፍ/ቤቱ ዕግድ በኋላ ወይንስ በፊት? የሸጠውስ በምን ያህል ነው? የሚለውን በሚስጥር ይዞ ስለማቆየቱና ክርክሩም በማስረጃ የተደገፈ እንዳልሆነ ገልጿል ከማለት በቀር አመልካች ወርቁን የሸጠው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እንዳይሸጥ የሚል የዕግድ ትዕዛዝ ከሰጠና ከደረሰው በኋላ ነው በሚል በግልጽ ያቀረበው ክርክር የለም በግልጽ ያልተካደ ፍሬ ነገር ደግሞ በሕጉ እንደታመነ የሚቆጠር ነው፡፡

አመልካች በኤግዚቢትነት ይዞ የቆየውን የአፈር ወርቅ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ወርቁ እንዳይሸጥ በማለት የዕግድ ትዕዛዝ ከመስጠቱ በፊት አስቀድሞ የፌዴራል የመጀመሪያ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪን በወንጀሉ ጥፋተኛ በማድረግ ወርቁ ይወረስ ብሎ በሰጠው የውርስ ወሣኔ መሠረት የሸጠው መሆኑ የታመነ ሆኖ ከተገኘ አመልካች ለተጠሪ ለመክፈል የሚገደደው በወቅቱ ወርቁን የሸጠበትን ዋጋ ነው፡፡

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን በይግባኝ አይቶ ተጠሪን ከወንጀል ክሱ በነፃ በማሰናበት ወርቁ ይመለስለት ብሎ ባዘዘበት ጊዜ በነበረው የገበያ ዋጋ መከፈል አለበት በሚል የቀረበው ክርክር በሕጉ ተቀባይነት የሚሰጠው አይደለም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ረገድ የሰጡት ውሣኔም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስለተገኘ ሊታረም የሚገባው ነው፡፡ በዚህም ምክንያት የሚከተለው ተወስኗል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1ኛ) የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ/43191 የካቲት 29 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እና

2ኛ) የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የኮ/መ/ቁ. 90395 ሰኔ 16 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ ተሻሽሎ የአሁኑ አመልካች በኤግዚቪትነት ተይዞ የቆየውን 2512 ግራም አፈር ወርቅ በወቅቱ የሸጠበትን ዋጋ ለአሁኑ ተጠሪ እንዲከፍል ተወስኗል፡፡

3ኛ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በዚህ ውሳኔ መሠረት እንዲያስፈጽም ታዟል፡፡ ይፃፍ፡፡

4ኛ) በዚህ መዝገብ የተሰጠው ፍርድ ትክክለኛ ግልባጭ ይተላለፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ ፡፡

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡*

እ/ብ